# አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ)

# የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ

## መግቢያ

አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ (ከዚህ በኃላ "ማህበሩ" እየተባለ የሚጠራው) አደራጆቹ የመድን ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 86/1986 እና በ1952 ዓ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 166/1952 የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተው በወቅቱ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት ተብሎ ይጠራ በነበረው ተቋም በቀን 21/10/1999 ዓ.ም አስመዝግው ስራ ላይ እንዲውል አድርገው የነበረ ቢሆንም፤

አክሲዮን ማህበራትን በሚመለከት በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 166/1952 ላይ የተደነገጉት ሕግጋት ተሽረው በ2013 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 (ከዚህ በኃላ "የንግድ ሕግ" እየተባለ የሚጠራው) በመተካታቸው፤

ይህ የተሻሻለው የንግድ ሕግም የማናቸውንም አክሲዮን ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ እውቅና የማይሰጥ ሲሆን፣ ሆኖም ማህበሩ የማህበሩንና የአስተዳደር አካላትን ተግባራትና ኃላፊነት የሚወስን ዝርዝር መተዳደሪያ ደንብ ያለው በመሆኑ፤ እነዚህን የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች ከነማሻሻያዎቻቸው በመመስረቻ ጽሁፉ ውስጥ ማጠቃለል በማስፈለጉ፤ እና

በመመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ማጣቀሻ ድንጋጌዎች፣ ቃላትና ሐረጎችን ከተሻሻለው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ማስተካከያ ማድረግ፤ እንዲሁም በዚህ ንግድ ሕግ ማሻሻያ ከተደረገባቸው ድንጋጌዎች አንፃር በመመስረቻ ጽሁፉ እንደ አዲስ ሊካተቱ የሚገባቸውን ድንጋጌዎች ማካተት በማስፈለጉ፤

ስለሆነም እኛ ከዚህ በታች በአንቀጽ ሦስት ሙሉ ስማችን፣ ዜግነታችን እና አድራሻችን የተገለጸው አባላት (ከዚህ በኋላ "ባለአክሲዮኖች" ተብለን የምንጠራ) ታህሳስ 20/2016 ዓ.ም ባደረግነው የባለአክሲዮኖች 7ኛ አስቸኳይ ጉባኤ የማህበሩን የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ /ከነማሻሻያዎቻቸው/ በአንድ ላይ በማጠቃለል እና በማሻሻል በንግድ ህግ አንቀጽ 400 (1) መሠረት ይህን የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፍ አጽድቀነዋል፡፡

## አንቀጽ አንድ፡
## የማህበሩ መጠሪያ ስም

የማህበሩ መጠሪያ ስም "አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ)" ነው፡፡

## አንቀጽ ሁለት፡
## የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች

2.1. የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻው ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ ከተማ፣ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 04፣ የቤት ቁጥር 049 /አንበሳ ኢንሹራንስ ህንፃ/ ይሆናል፡፡

2.2. ማህበሩ እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን ፍቃድ ከሚመለከተው አካል ሲያገኝ በኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ተጨማሪ ቅርንጫፎች እና ተጠሪ ጽ/ቤቶች ሊከፍት/ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሦስት፡
## የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ

የማህበሩ ባለአክስዮኖችን ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የፈረሙትን አክሲዮን ብዛትና የከፈሉትን የገንዘብ መጠን ብዛት የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ በማህበሩ የባለአክሲዮን መዝገብ የተገለፀውን ይሆናል፡፡ (የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ ሰነድ) ከዚህ መመስረቻ ፅሑፍ ጋር አባሪ የተደረገ ሲሆን፣ ይህም ሰነድ የዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አካል ነው፡፡

## አንቀጽ አራት፡
## የማህበሩ የንግድ አላማዎችና የስራ መስክ

የማህበሩ የንግድ አላማዎችና የሥራ መስኮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

4.1. ማናቸውንም አይነት የጠቅላላ መድን ሥራ፣ የረጅም ጊዜ መድን ሥራ፣ እና የጠለፋ መድን ስራዎችን ማከናወን፤

4.2. ማህበሩ የሚሰራቸው የመድን ስራዎችን በተመለከተ ከመድንና ከጠለፋ ዋስትና ሰጪዎች ጋር መዋዋልና ህጉ በሚፈቅደው መሰረት መተግበር፤

4.3. የማህበሩ አላማዎችና የንግድ ሥራዎች በሚያጠናክሩ ተጓዳኝ በሆኑ በማናቸውም የንግድና የኢንቨስትመንት ሥራዎች መሳተፍ፤

4.4. የመድን ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ የማማከርና የስልጠና አገልግሎት መስጠት፤

4.5. የታካፉል እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች በህግ የተፈቀዱ የኢስላሚክ ፋይናንስ መድን አገልግሎት መስጠት፤

4.6. የማይክሮ መድን አገልግሎት መስጠት፤

4.7. አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የካፒተል ገበያ ሥራ መስራት/መሳተፍ፤

4.8. ማህበሩ ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ የባለሞተር ተሽከርካሪ ጥገናና ጉዳት ግምት አገልግሎት የሚሰጥበት ጋራጅ፣ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ማቋቋምና ማካሄድ፤

4.9. ማህበሩ ከሚያካሂዳቸው የመድን ሥራዎች ጋር በተያያዘ የአደጋ ሥጋት አስተዳደርና ጉዳት የማስተካከል ምክር አገልግሎቶች መስጠት፤

4.10. በኢንቨስትመንት የማማከርና ሀብት የማስተዳደር አገልግሎቶችን መስጠት፤
4.11. ንብረት በአደራ የማስቀመጥ ተግባር ማከናወን፤
4.12. የኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት አገልግሎት መስጠት፤
4.13. ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሌላ የመድን ስራ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲስፋፋ ተጨማሪ የመድን ስራዎችን ማከናወን፣ እና
4.14. አግባብነት ያላቸው ሕጎች በሚፍቅዱት መሠረት ከማህበሩ የንግድ ዓላማዎች ተዛማጅ የሆኑ ማናቸውንም የንግድና የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ማከናወን።

## አንቀጽ አምስት
## የማህበሩ ዋና ገንዘብ፤

5.1. የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ብር 288,146,900 /ብር ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ/ ነው።
5.2. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የተፈረመ የማህበሩ ዋና ገንዘብ እያንዳንዳቸው ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) ዋጋ ባላቸው 2,881,469 (ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ዘጠኝ) መደበኛና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው።
5.3. ከተፈረመው የማህበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለው ብር 288,146,900 /ብር ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ/ ነው።

## አንቀጽ ስድስት
## ስለአክስዮኖች

6.1. ማህበሩ ተመሣሣይ ዋጋ ያላቸው ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈሉ አንድ አይነት እና እኩል የሆኑ፣ ልዩ መብት የማይሰጡ የተመዘገቡና መደበኛ አክሲዮኖች ይኖሩታል።
6.2. ማንም ሰው ባለአክሲዮን ሆኖ ለመመዝገብ ቢያንስ 100 (አንድ መቶ) አክሲዮኖች መፈረም ይኖርበታል፤ ይህ የቁጥር ገደብ ስነባር ባለአክሲዮኖች የሚደረግ ዝውውርን አይመለከትም።
6.3. ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በፈረሙ ጊዜ ቢያንስ የፈረሙትን አክሲዮኖች 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ያህል ወድያውኑ መክፈል አለባቸው። አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው አዲስ አክሲዮን ሽያጭ በሚወሰንበት ጊዜ ወዲያውኑ መከፈል የሚኖርበትን የገንዘብ መጠን ከ25% (ሃያ አምስት በመቶ) በላይ እንዲሆን ሊወስን ይችላል።
6.4. የመድን ሥራ ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 746/2012 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለ) ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SIB/35/2013 መሰረት ማናቸውም ባለአክሲዮን/ፈራሚ፣ በአንድ ባለአክሲዮን በተናጠል ወይም ከሚስቱ/ባሏ ጋር ወይንም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ የሥጋ ዝምድና ከሚዛመዳቸው/ከምትዛመዳቸው ግለሰቦች ጋር በመሆን በባለቤትነት የሚያዙ የማህበሩ የተፈረሙ አክሲዮኖች ውስጥ ከአምስት በመቶ (5%) በላይ አክሲዮኖችን ሲበልጥ አይችልም።
6.5. አክስዮኖች በግዑዝ አልባ (በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ) ሊወጡ ይችላሉ። የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስነው መሰረት በወረቀት የወጡ አክስዮኖች በግዑዝ አልባ አክስዮኖች ሊተኩ ይችላሉ።

6.6. እያንዳንዱ በወረቀት የሚሰጥ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ተፈርሞ የማህበሩ ማሕተም ያረፈበት ሆኖ፣ በገፁ ላይ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል፡-

6.6.1. የማህበሩ ስም፣ የማህበሩ ዋና መ/ቤትና ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ፤

6.6.2. የማህበሩ ዋና ገንዘብና አክሲዮኑ የወጣበት ዋጋ መጠን፤

6.6.3. የመመስረቻ ጽሑፉ የተፈረመበት ቀን እና ማህበሩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቀንና የምዝገባው ቦታ፤

6.6.4. የአክሲዮን መለያ (ሲሪያል) ቁጥር እና አክሲዮኑ መደበኛና የተመዘገበ ስለመሆኑ፤

6.6.5. የአክሲዮኑ ዋጋ በሙሉ ካልተከፈለ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን ወይም ዋጋው በሙሉ ከተከፈለ ይህንኑ የሚያመላክት መግለጫ፤

6.6.6. አክሲዮኑ ለውጪ ዜጋ መተላለፍ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፡፡

6.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት የጠፋበት ባለአክሲዮን ስመጥፋቱ የሚያረጋግጥ ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል ሲያቀርብ በጠፋው ምትክ አዲስ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ሊሰጠው/ሊሰጣት ይችላሉ፡፡

6.8. የዳይሬክተሮች ቦርድ በጠፋው ምስክር ወረቀት ምትክ አዲስ ምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት፣ ተገቢ ነው በሚለው መንገድ ባለአክሲዮኑ የአክሲዮን ሰርተፍኬቱ ስለመጥፋቱ ማስታወቂያ እንዲያወጣና በጠፋው አክሲዮን ምክንያት በማህበሩ ላይ ሊቀርብ ለሚችል ክስና ማህበሩ ሊደርስበት ለሚችል ጉዳት ተመጣጣኝ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

6.9. አክሲዮኖቹ የማይከፋፈሉ ሲሆኑ፤ እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ አለው፡፡ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የአክሲዮን የጋራ ባለሀብት በሆኑ ጊዜ የባለቤትነት መብታቸውን የሚወክል ከመካከላቸው ወኪል መሾም አለባቸው፡፡ የአክሲዮኑ የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች እና ግዴታዎች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## አክስዮኖችን ስለመመዝገብ እና ስለማስተላለፍ

7.1. ማህበሩ የባለአክስዮኖችን ዝርዝር የሚያሳይ መዝገብ በዋና መስሪያ ቤቱ ይይዛል፤ መዝገቡ የወረቀት ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ቋሚ የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ሊሆን ይችላል፡፡

7.2. መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስምና አድራሻ፣ ዜግነት፣ የአክሲዮኖችን መለያ ቁጥርና ብዛታቸውን፣ የተከፈለውን ዋና ገንዘብ መጠን እና ባለአክሲዮኖቹ በመዝገቡ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፡፡

7.3. መዝገቡን ማናቸውም ባለአክሲዮን እንዲሁም የተፈቀደለት አካል መመልከት እንዲችል በማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሁሉ ክፍት መሆን አለበት፡፡

7.4. አክሲዮኖችን በዋስትና ማስያዝን ጨምሮ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ማዘዋወር ወይም በባለመብትነት ለሌሎች መስጠት በአዋጅ ቁጥር 1147/2011 ላይ የተቀመጠው የህግ መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በማህበሩ በተዘጋጅው መዝገብ ላይ ጭምር መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ እስከሚተላለፍበት ጊዜ ድረስ ይዞታው በቀድሞ ባለአክሲዮን ይቀጥላል፡፡

7.5. እያንዳንዱ የተመዘገበ አክሲዮን ዝውውር ወይም ለሌላ ሰው ባለመብትነት መስጠት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ ስምንት
## የባለአክሲዮኖች መብቶች

8.1. የማህበሩን አክሲዮን በስሙ የያዘ ማንኛውም ባለአክሲዮን በስሙ የፈረመውንና የከፈለውን የአክሲዮን ዋጋ የያዘ በንግድ ህግ አንቀጽ 273 የተመለከቱትን ዝርዝሮች ያካተተ ሳምጨው ያልሆነ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ የተፈረመ የአክሲዮን ማህበሩ ምስክር ወረቀት ለባለአክሲዮኑ በስሙ ተዘጋጅቶና ተመዝግቦ የማግኘት መብት አለው፡፡

8.2. አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ውስጥ በስሙ የያዘውን አክሲዮን በሕግ መሰረት ለሦስተኛ ወገኖች የማስተላለፍ መብት አለው፡፡

8.3. አክሲዮኖችን በጋራ ባለቤትነት ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት፣ በአክሲዮኖቹ ላይ መብት የሚኖረው (የሚኖራቸው) በሕይወት የሚገኘው/የሚገኙት/ ባለአክሲዮን እና የሟቹ ወራሽ/ወራሾች/ ይሆናሉ፡፡

8.4. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 271/5/ መሰረት የማህበሩ አክሲዮኖች በዕዳ መያዣነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የመያዣ ውሉ በማህበሩ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

8.5. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 271/1/ አንድ አክሲዮን በመያዣ ወይም በአላባ መብት የተሰጠ እንደሆነ በባለአክሲዮኑና በመያዣ ወይም በአላባ መብት ተቀባይ መካከል ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች ድምጽ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

8.6. የማህበሩ ዋና ገንዘብ ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ የሚሸጡ አዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ ባለአክሲዮኖች አስቀድሞ በባለቤትነት በያዟቸው አክሲዮኖች መጠን ልክ ተደልድሎ አዲስ አክሲዮን በቅድሚያ የመግዛት መብት አላቸው፡፡

8.7. በሕግ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ባለአክሲዮን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 363፣ 397 እና 401 መሰረት በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ከባለአክሲዮንነት የሚመነጨውን በተለይ በስብሰባዎች የመሳተፍ፣ ድምጽ የመስጠት፣ የማህበሩን ውሳኔ የመቃወም እንዲሁም ትርፍ የመካፈል መብት አለው፡፡

8.8. በሕግ የተቀመጠውን መስፈርት ካሟላ ለቦርድ አባልነት ለምርጫ በእጩነት የመቅረብ፣ የቦርድ አባላትን የመምረጥ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በእንደራሴነት የመገኘት መብት አለው፡፡

8.9. በማህበሩ ጉባኤዎች ላይ ባለአክሲዮኖች በውክልና ሊወከሉ የሚችሉት ከኢፌዲሪ የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎት ወይም በማንኛውም ስያሜ ይህንን ተግባር ለመፈጸም ከተቋቋመ ተቋም በተመዘገበ ልዩ ውክልና፣ ወይም ባለአክሲዮኖች በጽሁፍ በሚሰጡት የእንደራሴነት ውክልና ወይም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 373/1/ እና 377 መሰረት ማህበሩ በሚያዘጋጀው የውክልና ፎርም ከጉባኤው እለት ሶስት ቀናት አስቀድሞ በማህበሩ ዋና መ/ቤት በማቅረብ ነው፡፡

8.10. ማንኛውም ባለአክሲዮን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 378 እና 381 መሰረት በስብሰባ የተሳታፊዎችን መመዝገቢያ ሰነድ ጨምሮ የማህበሩን ሰነዶች የማየት ወይም ግልባጭ በራሱ ወጪ የማግኘት መብት አለው፡፡

8.11. በንግድ ሕጉ አንቀጽ 291 /1 እና 2/ መሰረት ማንኛውም ባለአክሲዮን ትርፍ ተከፋይ የሚሆነው እና ማህበሩ በመክሰሩ ምክንያት የሚከፈለው ድርሻ ሲኖር ዋጋቸው ተሟልቶ በተከፈሉ አክሲዮኖች ላይ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ
## የባለአክሲዮኖች ግዴታዎች

9.1. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ግዴታዎች በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ፣ አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና ድንጋጌዎች መሰረት የተመለከቱት ናቸው፡፡

9.2. የተናጠል ወይም የጋራ ባለአክሲዮኖች በሕግ መሰረት ለማህበሩ ዕዳ ወይም ግዴታ ተጠያቂ የሚሆኑት በስማቸው በያዟቸው አክሲዮኖች ዋጋ መጠን ልክ በአንድነት እና በነጠላ ይሆናል፡፡

9.3. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ 289/1/ የተመለከቱት ሰዎች ሳልከፈሉት ቀሪ የአክሲዮን ሒሳብ እንዲከፈል በተወሰነው መክፈያ ጊዜ ውስጥ የመክፈል ግዴታ እና ኃላፊነት አለባቸው፡፡

9.4. አክሲዮኖቹን በአሳባ ጥቅም ያስያዘ ባለአክሲዮን የአሳባው ጊዜ ሲያልቅ ባለአሳባው ለማህበሩ የከፈለው የአክሲዮን ገንዘብ እንዲመልስ ያለበት ግዴታ ሳይነካ ያልተከፈለውን ቀሪ የአክሲዮን ገንዘብ በጥሪው መሰረት የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

9.5. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ከማህበሩ የተገኘ ብድርን በመጠቀም የማህበሩን አክሲዮን ሲገዙ አይፈቀድላቸውም፡፡

9.6. ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን ለመቀየር የሚፈልጉ ባለአክሲዮኖች አስቀድመው ለዳይሬክተሮች ቦርድ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

9.7. አክሲዮን በግል እና በጋራ በስማቸው የያዙ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.2 የተመለከቱ ባለአክሲዮኖች ሳልተከፈለው የአክሲዮን ዋጋ አከፋፈል ለተደረገው የማስጠንቀቂያ ጥሪ በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

9.8. ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.7 ስር ለተጠቀሱት ባለአክሲዮኖች የማስታወቂያ ጥሪ ሲያደርግ ያልተከፈሉ ቀሪ የአክሲዮን ብዛት ወይም መጠን እንዲሁም ቀሪ የገንዘብ መጠኑን ጭምር በመጥቀስ የተወሰነውን ክፍያ እንዲከፍሉ የመክፈያ የመጨረሻ ቀን በመግለጽ ለሚመለከተው እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ባስመዘገበው አድራሻ በጽሁፍ እንዲደርስ ጥረት በማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ከፍ ሲል የተገለጸውን ዝርዝር በያዘ መልኩ በኤሌክትሮኒክስ፣ በማህበሩ ድህረ-ገጽ እና በስልክ አጭር የጽሁፍ መልእክት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ በዚህ ጥሪ መገኘት ሳልቻሉ ባለአክሲዮኖች ከፍ ሲል የተጠቀሰውን አይነት ዝርዝር መያዝ ሳያስፈልገው ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ጥሪው እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

9.9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.8 ስር በተጠቀሰው አግባብ ቀሪው ሒሳብ እንዲከፈል የማስጠንቀቂያ ጥሪ ከተሰጠ በኋላ በተወሰነው ቀን ባልከፈለ ባለአክሲዮን የአክሲዮን ድርሻ ላይ በንግድ ሕግ ቁጥር 289/4/ መሰረት ማህበሩ አክሲዮኑን በሐራጅ ሽያጭ ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ አስር
## የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ

10.1. በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ፣ በመድን ስራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለ)፣ በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ተቀናሽ ሲደረጉ የሚገባቸው ሕጋዊ መጠባበቂያ ሒሳብና የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው የሚስማማባቸው ሌሎች የመጠባበቂያ ሒሳቦች ተቀናሽ ከተደረጉ በኋላ ዓመታዊ የማህበሩ የተጣራ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው ባላቸው የተከፈለ የአክሲዮን ብዛት መጠን ይሆናል፡፡

10.2. የሚከፈለው ትርፍ በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አቅራቢነት በማህበሩ ኦዲተሮች የተረጋገጠና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ የተጣራ ትርፍ ይሆናል፡፡

10.3. ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በልዩ ሁኔታ በቅድሚያ የውጭ ኦዲተሮች አስተያየት በመቀበል ከመጠባበቂያ ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጎ የትርፍ ክፍፍል እንዲከፈል ሲፈቀድ ይችላል:: የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔም ለትርፍ ተከፋይ የሚሆኑት ገንዘቦች ከየትኛው መጠባበቂያ ገንዘብ ላይ እንደሚወሰዱ በግልፅ ማመላከት ይኖርበታል::

10.4. የትርፍ ድርሻ አከፋፈል በገንዘብ ወይም በአክሲዮን ለማድረግ ይቻላል::

10.5. በሕግ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር የትርፍ ድርሻ የሚከፈልበት ቀን ጠቅላላ ጉባኤ ከተደረገ በኋላ ባሉት የስራ ቀናት ይሆናል::

## አንቀጽ አስራ አንድ
## የማህበሩ አመራር አካላት

የማህበሩ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው::

11.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣
11.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
11.3. ዋና ስራ አስፈፃሚ /ዋና ስራ አስኪያጅ/፣
11.4. የማሕበሩ ፀሃፊ እና
11.5. የውጪ ኦዲተሮች

ከላይ የተመለከቱት የማህበሩ አመራር አካላት ሥልጣንና ተግባር በንግድ ሕግ፣ በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር746/2004፣ በመድን ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 1163/2012፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች እና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ በተወሰነው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል::

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን

12.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚሳተፉበት የማህበሩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፤

12.2. የማህበሩን ዓላማዎች፣ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፤

12.3. የማህበሩን ዋና ገንዘብ /ካፒታሉን/ መጨመር ወይም በሕግ ከተቀመጠው አነስተኛ መጠን ሳያልፍ የማህበሩን ዋና ገንዘብ/ ካፒታል/ መቀነስ ይችላል፤

12.4. ማህበሩ እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ ይወስናል፤ እንዲሁም ማህበሩ ህግ በሚፈቅደው መሠረት ከሌላ መድን ሰጪ ወይም የፋይናንስ ተቋም ወይም ድርጅት ጋር እንዲቀላቀል፣ እንዲዋሀድ ወይም ማህበሩ እንዲከፋፈል ሊወስን ይችላል፤

12.5. በንግድ ሕግ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የችሎታ መመዘኛ የሚያሟሉና የሕግ ክልከላ የሌለባቸው መሆኑ ሲያረጋግጥ ዳይሬክተሮችን ይሰይማል ይሽራል አበልና የሥራ ዋጋ ክፍያዎችንም ይወስናል::

12.6. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላ እና የምርጫ ኮሚቴ አባላት ይሾማል፤ አበልና ክፍያዎችንም ይወስናል፤ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና ምርጫ አፈፃፀም መመሪያ ያፀድቃል እንዲሁም ያሻሽላል::

12.7. በአክሲዮን የሚለወጡ የብድር ሰነዶች የሚፈቀዱበትን ሁኔታ ይወስናል፤

12.8. የማህበሩን ኦዲተሮች ይሾማል፣ ይሽራል፣ የስራ ጊዜያቸውንና የሚከፈላቸውንም የስራ ዋጋ ይወስናል::

12.9. የማህበሩን ሀብትና ዕዳ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ ሂሣብ እንዲሁም የዳይሬክተሮችንና የማህበሩ ኦዲተሮችን ሪፖርቶች መርምሮ ያጸድቃል ወይም ያልተቀበለው መሆኑን ያስታውቃል፡፡

12.10.ትርፍ ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ይወስናል ወይም አግባብነት ያለውን ሌላ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

12.11.በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰኑ ውሳኔዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች በስብሰባው ላይ ያልተገኙ፣ በውሳኔው ያልተስማሙ፣ ድምጽ ያልሰጡ ወይም ለመስጠት የማይችሉ ጭምር በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

12.12.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12.11. የተደነገገው ቢኖርም ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ ወይም ድምጽ የመስጠት መብቱ ላይ በሕግ፣ በፍ/ቤት ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተጣለ ገደብ ከሌለ በቀር ባለአክሲዮን በመሆኑ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን መሰረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባኤው ሊነፍገው አይችልም፡፡

12.13.አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉባኤው ሥልጣኑን በከፊል ለዳይሬክተሮች ቦርድ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## ስለ ጠቅላላ ጉባኤዎች

13.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ናቸው፡፡

13.2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሂሳብ ዓመቱ ከተዘጋ ባሉት 6 /ስድስት/ ወራት ውስጥ በዳይሬክተሮች ቦርድ መጠራት ያለበት ሲሆን፣ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውም ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መደረግ አለበት፤ ሆኖም የዳይሬክተሮች ቦርድ የተጣለበትን ኃላፊነት በማይወጣበት ጊዜ ጥሪውን የማህበሩ ኦዲተሮች ማድረግ አለባቸው፡፡

13.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣ ወይም በኦዲተሮች ሲጠራ፣ ወይም ቢያንስ ከማህበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ 10% (አስር በመቶ) ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ሲጠይቁ ወይም በፍ/ቤት ትእዛዝ የሂሳብ ዓመቱ ከማለቁ በፊት ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራና ሊካሄድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት
## የጠቅላላ ጉባኤዎች የጥሪ ማስታወቂያ፣

14.1. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ በንግድ ህግ አንቀጽ 367 የተደነገጉትን በሚያሟላ ሁኔታ መጠራት የሚኖርበት ሲሆን፤ ይህም አገር አቀፍ ስርጭት ባላቸው ሁለት ጋዜጦች እና በማህበሩ ድህር-ገጽ ጥሪው ከጉባኤው ቀን 24 /ሀያ አራት/ ቀናት በፊት ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ ባለአክሲዮኖች ባስመዘገቡት ኢሜይልና በስልክ አጭር የጽሁፍ መልእክት፣ ወይም ሌላ አስተማማኝ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ጥሪው ሊደረግ ይችላል፡፡

14.2. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪን ቀድሞ ለባለአክሲዮኖቹ ለማሳወቅ በንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 370 እና 371 በተደነገገው መሰረት የመጀመሪያው ጥሪ ስብሰባው ከሚደረግበት ቀን ሃያ አራት ቀናት በፊት ይደረጋል፡፡

14.3. ምልዓተ-ጉባዔ ባለመሟላቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መሰብሰብ ሳይችል የቀረ እንደሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሰበሰብ የሚደረገው ጥሪ የሚደረገው የመጀመሪያው ጉባዔ በሚጠራበት አኳኋን እና የጊዜ ገደብ ነው፡፡

14.4. ምልዓተ-ጉባኤ ባለመሟላቱ የተነሳ አንድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መደረግ ሳይችል ከቀረ ሁለተኛና ካስፈለገም ለሶስተኛ የጉባዔ ጥሪዎች በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 366 እና 367 በተመለከተው መሰረት ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት
## ስለ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ፣

የማህበሩ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

15.1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የማህበሩን ሀብትና ዕዳ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ ሂሣብ እንዲሁም የዳይሬክተሮችንና የኦዲተሮችን ሪፖርቶች መርምሮ ያጸድቃል ወይም ውድቅ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኦዲተሮች ሪፖርት ከቀረበለት በኋላ ሒሳቡን ያሻሽላል፣ በአክሲዮን የሚሰወጡ የዕዳ ሰነዶች የሚፈቀዱበትን ሁኔታና ከእነሱ ጋር የሚቀርቡትን ዋስትናዎች ያጸድቃል፡፡

15.2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበለትን የትርፍ ክፍፍል ተመልክቶ ትርፍ ሰባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ይወስናል ወይም አግባብነት ያለውን ሌላ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

15.3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እና ኦዲተሮችን ይሾማል፤ ይሽራል፤ አበላቸውንና የስራ ዋጋቸውን ይወስናል፡፡

15.4. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው በሕግ የአስቸኳይ ጉባዔው ሥልጣን ከሆኑት ውጭ በሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ተወያይቶ ይወስናል፡፡

15.5. ስመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው የሚስፈልግ ምልአተ ጉባኤና ድምፅ ብልጫን በተመለከተ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 398 የተደነገጉት ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## ስለ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ፣

የማህበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

16.1. የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍን ያሻሽላል፡፡

16.2. የማህበሩን ካፒታል ለማሳደግ ወይም ለመቀነስ በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚቀርብ ሃሳብ ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

16.3. የማህበሩን ዜግነት ስለመለወጥ፣ ማህበሩ እንዲፈርስ ወይም ወደሌላ አይነት የንግድ ማሕበር እንዲለወጥ፤ እንዲከፋፈል እና እንዲዋሃድ በሚቀርብ ሃሳብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

16.4. ሌሎች በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲታዩ ተለይተው በተሰጡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

16.5. ስአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የሚያስፈልግ ምልአተ ጉባኤና ድምፅ አሰጣጥን በተመለከተ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 402 የተደነገጉት ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት
## የጥቅም ግጭት

17.1. በእራሱ ስም ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን ስም በጉባኤው ላይ የሚገኝ ተሳታፊ ከማህበሩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ወይም በሕግ ወይም በፍ/ቤት ድምጽ የመስጠት ገደብ የተደረገበት በሆነ ጊዜ ተሳታፊው በቀረበው ጉዳይ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

17.2. ዳይሬክተሮች የራሳቸውን ኃላፊነት እና ግዴታ በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምፅ አይሰጡም፡፡

17.3. ምልዓተ-ጉባኤ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀፅ ውስጥ ድምፅ የመስጠት መብት የተነፈጋቸው /የተከለከሉ/ አክሲዮኖች ከቁጥር ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

17.4. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የተደነገገ፣ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 289(7) እንዲሁም ከዚህ ቀደም ብለው ባሉት በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፆች 17.1-17.3 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው፤ በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ ድምፅ በመስጠት መብት በነፃ መጠቀምን የሚቀንስ ማናቸውም ድንጋጌ አይፀናም፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## የዳይሬክተሮች ቦርድ

18.1. ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤው በሚሰየሙ ዘጠኝ /9/ አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡

18.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና ምርጫን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

18.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ፣ በዚህ የመመስረቻ ፅሑፍ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማህበሩ ሌላ አካል (ሌሎች አካሎች) ተለይተው ከተሰጡ ሥልጣኖች በስተቀር የማህበሩ ድርጅታዊ ሥልጣኖች ይኖሩታል፡፡

18.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለሌላ ለማህበሩ አመራር አካል ተለይቶ የተሰጠ ስልጣን ካልሆነ በስተቀር የማህበሩ ድርጅታዊ ሥልጣኖች ይኖሩታል፡፡

18.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የአንድ ዙር የአገልግሎት ዘመን 3 (ሦስት) ዓመታት ሲሆን፤ አንድ አባል መመረጥና ማገልገል የሚችለው ለሁለት ተከታታይ ዘመን ማለትም ለ6 (ስድስት) ዓመታት ብቻ ነው፡፡

18.6. የዚህ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ለሥራ ቀጣይነት አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ 2 (ሁለት) የምርጫ ዘመን ያገለገሉት የቦርድ አባላትን ለተጨማሪ 1 (አንድ) ዙር ማለትም ለሦስተኛ ዙር እንዲመረጡ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ሊወሰን ይችላል፡፡ ሆኖም ለተጨማሪ 1 (አንድ) ዙር የሚመረጡ የቦርድ አባላት ብዛት ከጠቅላላ ቦርድ መቀመጫ ከ1/3ኛ (ከአንድ ሶስተኛ) መብለጥ የለበትም፡፡

18.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ከአባላቱ ¾ በተገኙበት ስብሰባ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢን እና ምክትል ሰብሳቢን በአብላጭ ድምፅ ይመርጣል፡፡

18.8. በንግድ ህጉ አንቀጽ 304 መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ወርሃዊ አበል እና ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡ ይህም ዓመታዊ አገልግሎት ክፍያ ለቦርዱ የሚፈጸመው ማህበሩ በሂሳብ አመቱ የተጣራ ትርፍ ካገኘ እና ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

18.9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 17 ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሲፈቅድ ጠቅላላ ጉባኤው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 304/2/ መሰረት ከማህበሩ የዓመቱ የተጣራ ትርፍ ላይ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ጉርሻ እንዲከፈላቸው መጠኑን ሊወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን እና ተግባራት

19.1. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 18.4 የተጠቀሰው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-

- 19.1.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በመመሥረቻ ጽሑፍ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች መሰረት የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
- 19.1.2. የማህበሩን ሥራ አመራር በበላይነት ይቆጣጠራል፤
- 19.1.3. የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ ይሾማል፣ ያሰናብታል፤ ሥልጣኑንና ተግባሩን እንዲሁም ደመወዝ እና ሌሎች ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማጥቅሞችንም ይወስናል፤
- 19.1.4. የማህበሩ የውስጥ ኦዲት እና የሪስክ ማናጅመንት ከፍተኛ የስራ መደቦች የበላይ ኃላፊዎችን ይሾማል፣ ያሰናብታል፤
- 19.1.5. የማህበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ /ዋና ስራ-አስኪጅ/ የሚያቀርባቸውን ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑ የማህበሩ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎችን እና የማሕበሩ ፀሐፊን ሹመት እና ስንብት ያጸድቃል፤ የሥራ ሁኔታዎችንም ይወስናል፤
- 19.1.6. የማህበሩን ስትራቴጂዎች፣ ፖሊሲዎች፣ ሲስተሞች፣ ድርጅታዊ መዋቅርና አደረጃጀት፣ የስትራቴጂክ እቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት እና የሠራተኛች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም፤ በዋና ስራ-አስፋጻሚ ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት በአግባቡ አይቶና ካስፈለገም ከልሶ ያጸድቃል፤ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፡፡
- 19.1.7. የማህበሩ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን ይሠጣል፤ እንዲሁም እርምጃዎች ይወስዳል፤
- 19.1.8. ከኢትዮጵያ ውጪ ስለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ውሳኔ ይሰጣል፡፡
- 19.1.9. በዋና ስራ አስፈፃሚ የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንትና የቋሚ ንብረት እና የቴክኖሎጂ ግዥ ጥያቄዎችን ያፀድቃል፡፡
- 19.1.10. የማህበሩን ገንዘብ በሕግ በተፈቀዱ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ያውላል፤ መዋላቸውንም ይቆጣጠራል፤
- 19.1.11. የዳይሬክተሮች ቦርድ የማይንቀሳቀሱ ወይም የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የመግዛት፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማስተላለፍ፣ በዕዳ መያዣነት ወይም በዋስትና የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባኤ ለዋና ስራ-አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
- 19.1.12. የማህበሩን የንግድ አላማ ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ከዋና ስራ አስፈፃሚው ጋር በመሆን በማህበሩ ስም በዋስትናም ሆነ ያለ ዋስትና ገንዘብ መበደር ይችላል፤ ቦርዱ በዋስትና የመበደር ሥልጣኑን በቃለ-ጉባኤ ለዋና ስራ-አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
- 19.1.13. ማህበሩ የእዳ ሰነዶችን እንዲያወጣ ይፈቅዳል፤ ከዚህ ጋር የተያያዘ የሚሰጥ ዋስትና ላይ ይወስናል፤
- 19.1.14. የቦርዱን ሥራ በአማካሪነት የሚያግዙ በክፍያም ሆነ ያለክፍያ የሚሰሩ ግለሰቦች ያሉት ቡድን እንደ አስፈላጊነቱ ያዋቅራል፣ የአባላቱን ደሞዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይወስናል፤
- 19.1.15. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣኑን በከፊል ለቦርዱ አባል ወይም ለማህበሩ ዋና ስራ-አስፈፃሚ ሊሰጥ ይችላል፤

19.1.16. ሕጉ በሚያዘው መሰረት የማህበሩ የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፤ በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

19.1.17. የማህበሩን ሂሣቦች በማህበሩ ኦዲተሮች እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡ ስለማህበሩ የሂሣብ መግለጫ ዓመታዊ ሪፖርት ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤

19.1.18. የማህበሩ ¾ (ሦስት አራተኛ) ካፒታል የጠፋ እንደሆነ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጉባዔ ሳይዘገይ ይጠራል፤

19.1.19. በሕግና በመመስረቻ ጽሑፉ መሰረት መያዝ ያለባቸውን መጠባበቂያ ገንዘቦች እንዲያዙ ያደርጋል፤

19.1.20. ማህበሩ በኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 274(1 እና 2) እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት የሚወሰኑ ዝርዝሮችን ያካተተ የባለአክሲዮኖች መዝገብ ማደራጀት/ማዘጋጀትና በዋናው መ/ቤት መያዙን ያረጋግጣል፡፡

19.1.21. በሌሎች በህግና በባለአክሲዮኖች ጉባዔዎች የተወሰኑትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

19.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት ለማህበሩ በአንድነት እና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

19.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በተገቢው ጥንቃቄ እና ትጋት ስለመስራታቸው የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እና ውሳኔዎች፤

20.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቦርዱ ስብሰባዎችን አስመልክቶ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ቢያንስ በወር 1 (አንድ) ጊዜ ስብሰባውን ያካሂዳል፡፡

20.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎችን በሰብሳቢው ወይም ሰብሳቢው በማይኖሩበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው እየተመራ ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው በሚሰየም በማናቸውም ዳይሬክተር ይመራል፡፡

20.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰብሳቢዎችን ማንነት መለየት በሚያስችል እንዲሁም የአባላት ውጤታማ ተሳትፎን በሚያረጋግጥ መልኩ ስብሰባዎችን ቪዲዮ ኮንፈረንስ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ማካሄድ ይችላል፤ የቦርድ አባላትም የቪዲዮ ኮንፈረንስ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ስብሰባዎችን መሳተፍ ይችላሉ፡፡

20.4. በቦርድ ስብሰባ ሲገኝ ያልቻለ ዳይሬክተር ሊወከል የሚችለው በሌላ ዳይሬክተር ብቻ ሲሆን፣ ውክልናውንም በደብዳቤ ወይም በኢሜል መልእክት ሊሰጥ ይችላል፡፡

20.5. ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈው ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ውክልናን ጨምሮ 5 (አምስት) ዳይሬክተሮች ሲገኙ ወይም ሲሳተፉ ነው፡፡

20.6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 20.5 የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በቪዲዮ ኮንፈረንስ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚካሄድ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤው እስከተሟላ ድረስ፣ በዚህ ስብሳባ ላይ የተሳተፉት ሁሉም ዳይሬክተሮች በአካል በስብሰባው ላይ ባይገኙም በስብሰባው ያስተላለፉት ውሳኔ የጸና ይሆናል፡፡

20.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ የሚተላለፍ ሲሆን ድምፅ በተወካይ ሊሰጥ ይቻላል፡፡ ድምፅ እኩል በእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

20.8. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባኤ ተይዘው በስብሰባው በተገኙ ዳይሬክተሮችና በማሕበሩ ፀሐፊ መፈረም አለበት፡፡ ቃለ ጉባኤዎች በቃለ ጉባኤ መዝገብ ውስጥ ተመዝግበው ይቀመጣሉ፡፡

20.9. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን ለማድረግ አጋዥነቱ አስፈላጊ ነው ብሎ በገመተ ጊዜ ሁሉ በባለሙያዎች ምክር ሊረዳ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## ዳይሬክተሮችን ስለመተካት

21.1. የዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 12.5 ድንጋጌ ቢኖርም፣ በአንድ ሂሳብ ዓመት ውስጥ አንድ ወይም ከዚህ የሚበልጡ ዳይሬክተሮች በአንቀጽ 21.3. ላይ በተመለከቱት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት የለቀቁ እንደሆነ ያሉት ዳይሬክተሮች ለቀሪው የሹመት ጊዜ የሚሸፍኑ ተተኪ ዳይሬክተሮችን በሕግ አግባብ መሰረት ሊሾሙ ይችላሉ፡፡ የተተኪ ዳይሬክተሮች ሹመት ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጠቅላላ ጉባዔውም ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮችን ሊሾም ይችላል፡፡

21.2. በማናቸውም ጊዜ የዲሬክተሮች ቁጥር ከ5 (አምስት) በታች በሚሆንበት ወቅት የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተጠርቶ አዲስ ዳይሬክተሮች ይሾማል፡፡

21.3. በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከዳይሬክተርነት ሊወገድ ይችላል፡፡

21.3.1. ዳይሬክተሩ ራሱ ወይም በዳይሬክተርነት ወይም በዋና ስራ አስፈፃሚነት የሚያገለግልበት ማህበር ሲከስር ወይም ዕዳ መሸፈን ሲሳነው፣ ወይም ዕዳውን ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ ሲወረስበት፤

21.3.2. የአዕምሮ ዕክል እንዳለበት ሲረጋገጥ ወይም በወንጀል በሚያስከስስ ጥፋት ሲፈረድበት፣

21.3.3. ካለልዩ ፈቃድ በሂሳብ አመቱ ውስጥ በተካሄዱ የዳይሬክተሮች ቦርዱን ስብሰባዎችን ቢያንስ 75% (ሰባት አምስት በመቶ) መሳተፍ ካልቻለ፤

21.3.4. በዳይሬክተሮች ቦርድ የስነምግባር ደንብ ወይም በስብሰባ አካሄድ ስርዓት ላይ በተጠቀሱ ወይም በሌሎች ማናቸውም ምክንያቶች፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት

## የዋና ስራ አስፈፃሚ ስልጣን እና ተግባራት፤

22.1. ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ /ዋና ስራ-አስኪጅ/ የሚኖረው ሲሆን፤ ዋና ስራ አስፈጻሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች እና ከኃላፊነት ስለመታገድ ዝርዝር ሁኔታዎች በመድን ስራ አዋጁ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

22.2. የማህበሩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወሰኑትንና የሚሰጠውን አጠቃላይ አመራር ተከትሎ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

22.2.1. ማህበሩ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት፣ ከመንግስታዊና የግል ድርጅቶች እንዲሁም ከሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርገውን የሥራ ግንኙነት ይወክላል፡፡

22.2.2. ማህበሩን በዓለም አቀፍ ደረጃ በመወከል ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ውል ይዋዋላል፤ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር የጠለፋ ዋስትና ኩባንያዎች ጋር ይደራደራል፤ ውል ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፡፡

22.2.3. በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ውሳኔ ይሰጣል፡፡

22.2.4. የመመስረቻ ጽሁፉ አንቀጽ 19.1.4 እና 19.1.5 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆነው፤ የማህበሩ ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፡፡

22.2.5. ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የማይንቀሳቀሱ ወይም የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ይሰውጣል፣ ያስተሳልፋል፣ የዕዳ መያዣነት ወይም የዋስትና ውል ይፈራረማል፡፡

22.2.6. በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 19.2.7 እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 22.5 ስር የተገለጹት ቢኖርም፤ በአንቀጾቹ ከተመለከቱት የውል አንቀጾች እና ሕግ በሌላ አኳኋን ክልከላ ካደረገባቸው ስራዎች ውጪ ያሉ ከመድን ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የቤት ኪራይ ውል መዋዋል፣ የመያዣ ውል መዋዋል፤ የማህበሩን ሕንጻ ማከራየት፣ ውክልና መስጠትን እንዲሁም የወደሙ እና ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ተሽከርካሪዎች፣ በአገልግሎት ብዛት ሲወገዱ ወይም ሲሸጡ የሚገባቸውን የማህበሩን ተሽከርካሪዎች ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ስራን፣ እና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ውሎች ዋና ሥራ አስኪያጁ በራሱ ሊፈጽም ይችላል፡፡

22.2.7. የማህበሩን የንግድ አላማ ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ከዳይሬክተሮች ቦርድ ጋር በመሆን በማህበሩ ስም በዋስትናም ሆነ ያለ ዋስትና ገንዘብ መበደር ይችላል፤ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የማህበሩን ንብረት በማስያዝ የብድር ውል ይዋዋላል፡፡

22.2.8. የማህበሩን ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ሲስተሞችን፣ ድርጅታዊ መዋቅርና አደረጃጀት፣ የስትራቴጂክ እቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት እና የሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም፤ በተመለከተ በማስጠናት ወይም በማርቀቅ ወይም ምክረ ሀሳብ በማዘጋጀት የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲያፀድቃቸው ያቀርባል፤ ሲፈቀዱ በአግባቡ ተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ይቆጣተራል፡፡

22.2.9. ዳይሬክተሮች ቦርድ ያወጣቸውን ፖሊሲዎች ተንተርሶ የሚወጡ የማህበሩ የአሰራር ደንቦች እና የሥነ-ስርአት ሕጎችን ያፀድቃል፤

22.2.10. የማህበሩ የሂሣብ አያያዝ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ የማህበሩን ዕለት ከዕለት ሥራ ለማከናወን የአመራር ስብሰባዎችን ይጠራል፣ ኮሚቴዎችንም ያቋቁማል፣ ለሥራ ኃላፊዎችና ለሰራተኛች ውክልና ይሰጣል፤

22.2.11. በማህበሩ ስም ወኪሎችን፣ የህግ አማካሪዎች፣ ነገረፈጆች እና ጠበቆች በመሾም/በመቅጠር የውክልና ሥልጣን ይሰጣል፤

22.2.12. በሕግና በዚህ የመመስረቻ ፅሑፍ ደንብ በተደነገጉት መሠረት የመጠባበቂያ ገንዘብ ሂሣቦች ያቋቁማል፤

22.2.13. በማህበሩ ስም ማንኛውም አይነት የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ውክልና በመስጠትም እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤

22.2.14. የሐዋላ ሰነዶችን፣ ቼኮችን፣ የሂሳብ ሠነዶችን፣ የምንዛሪ ሠነዶችን፣ የተፃፉ ሰነዶችን፣ ሌሎች የስምምነት ሠነዶችንና እንዲሁም የገቢና የወጪ ሠነዶችን ይፈርማል፣ ይቀበላል፣

22.2.15. ማህበሩን ከኪሣራ፣ከጥፋት፣ከድንገተኛ አደጋና ከማንኛውም ተጠያቂነት ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከማንኛውም የመድን ኩባንያ ጋር ተፈራርሞ ያስገባል፤

22.2.16. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ በሚወስነው መሰረት ከማህበሩ ዓላማዎች ሳይወጣ በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ስራ ላይ ያውላል፤

22.2.17. በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎችን በወቅቱ በማጠናቀቅ፣የማህበሩን የሂሣብ ሚዛንና የትርፍ የኪሣራ ሂሣብ በማዘጋጀት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፤

22.2.18. በዚህ መተዳደሪያ ደንቦች ውስጥ መደረግ ስለሚስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ ያቀባል፤

22.2.19.በዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ሲጠየቅ ከማህበሩ ፀሐፊ ጋር በመተባበር የቦርድ ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

22.2.20.ከቦርድ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር እና ከማህበሩ ፀሐፊ ጋር በመተጋገዝ የቦርድ ስብሰባዎችን ዝግጅት ያስተባብራል፤

22.2.21.በአጠቃላይ በዚህ ሠነድ በተለይ ያልተጠቀሱ እና በዋና ሥራ አስፈፃሚው /ዋና ስራ-አስኪያጁ/ የሥራ ኃላፊነት የሚወድቁ ወይም በግልጽ ከተሰጡት የሥራ ኃላፊነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የማህበሩን ዓላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ሥራዎች ያከናውናል፡፡

22.3. ዋና ስራ አስፈፃሚው ከላይ ከተሰጡት ሥልጣናት ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማህበሩ ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሦስት
## የማህበሩ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

23.1. ማህበሩ በዋና ሥራ አስፈፃሚ አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ የማህበር ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

23.2. እንደአስፈላጊነቱ የማህበሩ ፀሐፊ በሙያው ዋና ስራ አስፈፃሚውን እና የዳይሬክተሮች ቦርድን ሊያማክር ይችላል፡፡

23.3. እንዲሁም በንግድ ሕግ አንቀጽ 341 መሰረት፡-

23.3.1. የማህበሩን መረጃዎችና መዛግብቶች ያደራጃል እንዲሁም ይይዛል፤

23.3.2. ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ ይሰጣል፣

23.3.3. ለባለአክሲዮኖችና ለሦስተኛ ወገኖች መረጃ ይሰጣል፣

23.3.4. የባለአክሲዮኖችንና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች ያዘጋጃል፣

23.3.5. ቃለጉባኤዎችን ያዘጋጃል፣ አደራጅቶ ይይዛል፤ እና

23.3.6. በተጨማሪም በማህበሩ ዋና ሥራ ስራ አስፈጻሚ እና በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት
## የማህበሩ ኦዲተሮች

24.1. ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ አቅራቢነት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም ኦዲተር ይኖረዋል፡፡ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቀርቦ የሚጸድቅ የማህበሩን ኦዲተሮች ይሾማል፡፡ የተሾሙት ኦዲተሮችም ቢያንስ እስከሚቀጥለው የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ድረስ በሥራ ላይ መቆየት ይገባቸዋል፡፡ ይሁንና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የተሾሙ ኦዲተሮች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 344/2/ መሰረት ለሦስት ተከታታይ ዓመት እንዲያገለግሉ ጠቅላላ ጉባኤው ማጽደቅ ይችላል፡፡

24.2. የማህበሩ ኦዲተሮች ሥልጣንና ተግባር፣ ተጠያቂነት እንዲሁም የአበል ክፍያ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ በመድን ሥራ አዋጅ ቁጥር 746/2004 (በአዋጅ ቁጥር 1163/2012 እንደተሻሻለ)፣ በኦዲት ሥራ አዋጆች፣ በፋይናንስ ሕጎች፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች፣ በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ፣ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚያሳልፈው ውሳኔ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ይሆናል፡፡ ሪፖርቱም ከማህበሩ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኋላ ከ90 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መላክ አለበት፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት
## ስለማህበሩ ሒሳቦች

25.1. የመድን ስራ አዋጅ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸው መመሪያዎች የሂሣብና የመዛግብት አያያዝ በተመለከቱ ድንጋጌዎች በማህበሩ ሂሣብ አያያዝና አመዘጋገብም ላይ ተፈፃሚ ናቸው፡፡

25.2. ማህበሩ በተለይ የሚከተሉትን የማከናወን ኃላፊነት አለው፤

25.2.1. ጠቅላላ እና የረጅም ጊዜ የመድን ሥራ አገልገሎት በሚሰጥበት ለእንዳንዱ አብይ የመድን ስራ ወጪና ገቢን የሚያሳይ የሒሳብ መዝገብ መያዝ እና ቴክኒካዊ መጠባበቂያዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

25.2.2. ማህበሩ በመድን ሥራ አዋጅ እና በሌሎች ሕግጋት መሠረት መሥራቱን ለማወቅ የሚያስችሉ የማህበሩ ሥራ እንቅስቃሴዎቹንና ያለውን የገንዘብ አቅም ግልፅ በሆነና በትክክል የሚያስረዱ መዝገቦችን በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፤

25.2.3. ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለማህበሩ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ እና የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት መላክ አለበት፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት
## ሂሣብ ዓመት

የማህበሩ የሂሳብ ዓመት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሰባት
## ዓመታዊ ሪፖርት

27.1. በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት ማብቂያና በህግ እና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ መሠረት ለሚቀርበው ሪፖርት የዳይሬክተሮች ቦርድ፡

27.1.1. የትርፍና ኪሳራ ዝርዝር መግለጫ፣ የንብረት ቆጠራና የንብረትና የዕዳ ግምት ያዘጋጃል፡፡

27.1.2. እንደዚሁም ያለፈውን የሂሳብ ዓመት የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ ሂሣብ መግለጫ፣ በተጨማሪም ማህበሩ ባለፈው የሂሳብ ዓመት ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎችን የነበሩት ጉዳዮች የሚገቡበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

27.1.3. ሪፖርቱ ትርፍና ኪሳራ፣ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚ እና ለኦዲተሮች የተከፈለ ጠቅላላ ክፍያ፣ የተሰጠ ብድር ወይም የተገባ ዋስትና የሚያመላክት መግለጫ፤ እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዓመታዊ ትርፍ አደላደል ሃሣቦችን ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስምንት
## የሒሳብ ሰነዶችና ሪፖርት ለኦዲተሮች ስለማቅረብ

በንግድ ሕግ አንቀጽ 427 መሰረት የማህበሩ የንብረት ቆጠራ ዝርዝር፣ የሂሳብ ሚዛን የትርፍና ኪሳራ ሒሳብ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ጠቅላላ ጉባኤ ከመጠራቱ አርባ ቀናት በፊት ወይም በብሔራዊ ባንክ መመሪያ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ለኦዲተሮች እና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ

## መጠባበቂያ ሂሣብን ስለመያዝ

29.1. ማህበሩ በማናቸውም ጊዜ፡

29.1.1. በንግድ ሕጉ እና ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ማህበሩ የካፒታሉን የመጠባበቂያ ግዴታዎች ይይዛል፡፡

29.1.2. ዓመታዊ የትርፍ ክፍያ ድርሻ ከመገለፁ አስቀድሞ ከዓመቱ ትርፍ ላይ ታክስ ተነስቶለት ከሚቀረው የተጣራ ትርፍ ላይ ከአስር በመቶ (10%) ያሳነሰ ገንዘብ በመቀነስ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ያዛውራል፡፡ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ከማህበሩ ገንዘብ (ካፒታል) ጋር እኩል ሲሆን ከተጣራ ትርፍ ማህበሩ በየዓመቱ ለመጠባበቂያ የሚይዘው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንዲሆን ያደርጋል፡፡

29.1.3. ያልተከፋፈለ ትርፍ፣ የተያዘ ገቢና ሌሎች መጠበባቂያዎች አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ይፈፀማል፡፡

29.1.4. ማህበሩ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት መጠባበቂያዎች ውጪ በባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተወሰነ ከተጣራ ትርፉ ላይ ተቀናሽ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ ሊይዝ ይችላል፡፡

29.1.5. ከሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ተቀናሽ ማድረግ ወይም በመያዣነት መስጠት አይቻልም፡፡ ሆኖም የማህበሩ ካፒታል ለማሳደግ ሲባል በሕጉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ለካፒታል ማሳደጊያነት ማዋል ይቻላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ

## የሂሣብ ሚዛን መግለጫ ማውጣት

30.1. በባለአክስዮን ጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀው የማህበሩ የሀብትና እዳ መግለጫ አንድ ቅጂ እንዲሁም ጉባዔው መግለጫውን ያፀደቀበት ውሳኔ ቃለ-ጉባዔ አግባብ ያለው ክፍል የሀብትና እዳ መግለጫው በፀደቀ በ20 (ሃያ) የስራ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው የመንግስት አካል መላክ እና በማህበሩ ድረገፅ ላይ መውጣት አለበት፡፡

30.2. የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በተካሄደ በ2 (ሁለት) ሳምንታት ውስጥ ማህበሩ፡-

30.2.1. በኦዲተሮች የተመረመረ ሪፖርትና የስራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች በሁሉም የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት፣ ቅርንጫፎች ላይ ግልፅ በሆነ ቦታ እንዲሁም በማህበሩ ድህረ-ገጽ ያስቀምጣል፡፡

30.2.2. የሂሳብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ማብራሪያ ፅሑፎችን አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ያሳትማል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አንድ

## የማህበሩ የሥራ ዘመን

ማህበሩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሁለት
## ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች

በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ያልተገለጹ ሌሎች ሁኔታዎች አግባብነት ባላቸው ህጎች፣ በሙሉ በንግድ ሕግ፣ በመድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 746/2004፣ በመድን ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 1163/2012፣ እና በባለአክሲዮኖች ጉባዔ በሚተላለፉ ውሳኔዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሦስት
## ስለማህበሩ መፍረስ

33.1. ስለማህበሩ መፍረስ በተመለከተ አግባብነት ያላቸው ሕጎች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
33.2. ስለማህበሩ መፍረስ የተሾሙት ንብረት አጣሪዎች ተግባራቸውን አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ማከናወን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አራት
## የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ

የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህንን የመመሥረቻ ጽሑፍ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አምስት
## የማህበሩን ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ስለማሳደግና ስለመቀነስ

የማህበሩ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ በንግድ ሕግ፣ በመድን ሥራ አዋጅ ፣በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሰረት ሊያድግ ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ስድስት
## የዓይነት መዋጮ በማድረግ ካፒታሉን ስለማሳደግ

በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ የተመለከተው የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በንግድ ሕግ አንቀጽ 257 በተመለከተው የዓይነት መዋጮ ስርዓት መሰረት ካፒታል በዓይነት መዋጮ ሊያድግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሰባት
## የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ የመመስረቻ ጽሑፍ ከመፅደቁ በፊት በቀድሞ የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተከናወኑ ተግባሮች በሙሉ ህጋዊ ውጤታቸው የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ስምንት
## የተሻሻለው መመሥረቻ ጽሑፉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች 7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጸድቆ በሚመለከተው የመንግስት አካል ከተመዘገበ በኋላ በሥራ ላይ ይውላል፡፡